የስብሰባ ጥሪ
የዳያስፖራ ፖሊሲ ረቂቅ ውይይት

ለተከበራችሁ በቦስተንና በአካባቢዋ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ፤

በአሁኑ ወቅት ዳያስፖራው በአገሩ ላይ በተለያየ መልኩ አስተዋፅዖ በማድረግ አገሩን በመገንባትና ሕዝቡን በመርዳት ላይ ይገኛል። ከዚህም በመነሳት ዳያስፖራው ይህን በጎ ተግባሩን በተጠናከረ መንገድ ይቀጥል ዘንድ ከልምዶችና ተመክሮዎች በመነሳት የዳያስፖራው የፖሊሲ ረቂቅ ወጥቷል።

በዚሁ ረቂቅ ዙሪያ ለመወያየትና ረቂቁን በበለጠ ለማዳበር **Nov 27, 2011 ከቀኑ 10፡00 ሰዓት (4 PM) ጀምሮ በ 830 Tremont St. South End** ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣን በተገኙበት ውይይት ስለሚደረግ በዚሁ ቦታና ሰዓት ተገኝተው የውይይቱ ተሳታፊ ይሆኑ ዘንድ ተጋብዘዋል።

በተጨማሪ በዚሁ ዕለት ለህዳሴው ግድብ የሚውል የቦንድ ሽያጭ የሚደረግ መሆኑን ልናሳውቃችሁ እንወዳለን። የቦነዱ ግዥም ሂደት ይፋጠን ዘንድ በዕለቱ የቢጫ ካርድ (የተወላጅነት መታወቂያ ካርድ) ለማግኘት የሚያስችል ሂደትም ይካሄዳል። ቦንዱን ለመግዛት በቅድሚያ ቅጾችን ሞልተው ቢመጡ ሥራውን ያፈጥናል። በተጨማሪ የሚከተሉት ሰነዶች ይኑርዋ፤

1. 1 ጉርድ ፎቶ ለቦንዱና 3 ጉርድ ፎቶ ለቢጫው ካርድ
2. የልደት ምስክር ወረቀት ግልባጭ (Copy of Birth certificate)
3. የፓስፖርትዎን ግልባጭ (ኮፒ)

ሌላም ጥሩ ዜና

ባለፈው ወር በተደረገው የአባይ የህዳሴው ግድብ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ምሽት ለግድቡ መገንቢያ ይውል ዘንድ ወደ $100,000.00 ዶላር መሰብሰቡን በታላቅ ደስታ ልናበሥራችሁ እንወዳለን። ይህ የመጀመሪያችን ስለሆነ ጥሩ ውጤት ነው እንላለን። ሆኖም ግን የበለጠ ለመሥራትና የታሪክ ባላቤት ለመሆን እንችል ዘንድ እንረባረብበት እንላለን። ሥራው ተጀምሮአል፡፡ ለስኬቱ ትብብራችንን እናሳይ።

እንችላለን

በቦስተን የህዳሴው ግድብ አስተባባሪ ኮሚቴ